የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN CAPITAL MARKET AUTHORITY

ህዳር 17, 2018
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# ፈቃድ ሳያገኙ ቁጥጥር በሚደረግባቸው የካፒታል ገበያ ተግባራት ላይ ስለመሰማራት የተሰጠ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ እና ለህብረተሰቡ የተላለፈ ማሳሰቢያ

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪነት ፈቃድ ሳያገኙ በተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያዎች አማካኝነት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን (በተለይም የአክስዮን ማህበራት አክስዮኖችን) ለሽያጭ የማቅረብ፣ የማስተዋወቅ እና የማገበያየት እንቅስቃሴዎች እንደሚካሄዱ ተገንዝቧል። እነዚህ እንቅስቃሴዎች የካፒታል ገበያ አገልግሎት የሚሰጡ አካላት በባለስልጣኑ ተገቢውን ፈቃድ አግኝተው እና ቁጥጥር እየተደረገባቸው መሆን እንዳለበት በመደንገግ የወጡትን የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 እና የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 980/2016 የሚተላለፉ ናቸው።

ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኙ ቁጥጥር በሚደረግባቸው የካፒታል ገበያ ተግባራት ላይ መሰማራት በካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 አንቀጽ 106 ላይ በተደነገገው መሠረት እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ነው።

ባለስልጣኑም ፈቃድ ሳያገኙ በካፒታል ገበያ ተግባር እየተሳተፉ ያሉ አካላትን ለይቶ ለማወቅ ማህበራዊ ሚዲያዎችን እና ሌሎች መድረኮችን በንቃት እየተከታተለ የሚገኝ እና መረጃዎቻቸውንም አጠናቅሮ እየያዘ ሲሆን እነዚህ ያልተፈቀዱ እንቅስቃሴዎች በአስቸኳይ እንዲቆሙ እያሳሰብን የማይቆሙ ከሆነ ግን ባለስልጣኑ በእነዚህ እንቅስቃሴዎች በሚሳተፉ ግለሰቦች እና ቡድኖች ላይ ጠንካራ እርምጃዎችን እንደሚወስድ ለመጨረሻ ግዜ እያስጠነቀቀ፣ የካፒታል ገበያ አዋጁን በመጣስ የሚደረጉ ማናቸውም ድርጊቶች ከባድ ቅጣቶችን ሊያስከትሉ እንደሚችሉ እና ባለስልጣኑም የገበያውን ደህንነትና ታማኝነት ለማረጋገጥ ሙሉ ሕጋዊ ሥልጣኑን ከመጠቀም ወደኋላ እንደማይል ተገንዝባችሁ ከወዲሁ ከተግባራችሁ እንድትቆጠቡ እና የእርምት እርምጃ እንድትወስዱ ያሳስባል።

በዚህም ረገድ ህብረተሰቡ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲያደርግና በማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ለማገበያየት የሚያስተዋውቁ እና የሚያገበያዩ እንዲሁም የተለያየ የኢንቨስትመንት አማራጮችንና እድሎችን እናቀርባለን የሚሉ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ጋር ከመነጋገር እና ከመዋዋሉ አስቀድሞ ከባለስልጣኑ ተገቢው ፈቃድ ያለቸው መሆኑን እንዲያረጋግጥ ባለስልጣኑ ያሳስባል ።

የሰነደ ሙአለ ንዋይ ደላሎች፣ አሻሻጮች እና የኢንቨስትመንት አማካሪዎችን ጨምሮ ማንኛውም የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ከባለስልጣኑ ፈቃድ ማግኘት ያለበት ሲሆን፤ ፈቃድ የተሰጣቸው አገልግሎት ሰጪዎች የትኞቹ እንደሆኑ ለማወቅ የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣንን ይፋዊ ድህረ ገፅ https://ecma.gov.et/ በመጎብኘት ወይም በመስሪያቤቱ አድራሻ በአካል በመቅረብ መጠየቅና ማረጋገጥ ይችላሉ።

---

## ለተጨማሪ መረጃ እና ህገወጥ ደላላ እና አሻሻጮች ላይ ጥቆማ ለማቅረብ

**የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን፤** ፍላሚንጎ አካባቢ፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ፤ ምናዬ ኮርፖሬት ህንፃ 15ኛ ፎቅ፤ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
**ስልክ:** +251-11557-8250 እና +251-11557-8310
**ኢሜይል:** communication@ecma.gov.et